## የአሌክሳንድርያ የፎል/ጸደይ ወቅት ወደ ብስባሽነት መቀየር/ኮምፖስቲንግ!

በዚህ የፎል/ጸደይ ወቅት የከተማዋን ወደ ብስባሽነት መቀየር/ኮምፖስቲንግ ፕሮግራሞች እድሎችን ይጠቀሙ። የመንገድ ዳር የቆሻሻ መሰብሰቢያም ሆነ ቆሻሻ መጣያ በርካታ የተለያዩ አማራጮች አሉን።

### ለመንገድ ዳር (ከርብሳይድ) የምግብ ትራፊ ወደ ብስባሽነት መቀየሪያ የሙከራ ፕሮጀክት 2023-2025 ይመዝገቡ

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የቆሻሻ መጣያ እና መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል አገልግሎት ለሚያገኙ የከተማዋ ነዋሪዎች አዲስ የመንገድ ዳር የምግብ ትራፊ ወደ ብስባሽነት መቀየሪያ የሙከራ ፕሮጀክት ጀምሯል። ለሙከራ ፕሮጀክቱ የተፈቀደላቸው ነዋሪዎች እንደ የአትክልትና ፍራፍሬ ቁርጥራጮች፣ ስጋ፣ እና አጥንት ያሉ ነገሮችን ወደ ምግብ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ከማጣል ይልቅ ለምግብ ቆሻሻ ማከማቻ በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ማስቀመጥ ይችላሉ። **ዛሬውኑ ይመዝገቡ። ያሉን ቦታዎች ውስን ናቸው።**

ለመመዝገብ alexandriava.gov/FoodWaste የሚለውን ድረገጽ ይጎብኙ።

### በገበሬ ገበያዎች ውስጥ ዱባ እና ጃክ-ላንተርን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል

ለሃላዊን ያዘጋጁት ጃክ-ላንተርን እና ሌሎች ዱባዎች ወደ ብስባሽነት የሚቀየሩ ነገሮች ናቸው!

የእርስዎ ቀለም ካልተቀባ ሻማውን አውጥተው ከከተማው የገበሬ ገበያ የምግብ ቆሻሻ መጣያ ጣቢያዎች ወደ አንዱ ይውሰዱት።
አድራሻዎችን/ቦታዎች እና ሰዓታትን ለማወቅ alexandriava.gov/go/4299 የሚለውን ድረገጽ ይጎብኙ።

ለሚከተለው ክፍት ነው
የቅጠል መረጃ

የመጓጓዣ ክፍል እና
የአካባቢ አገልግሎት
301 King Street, Suite 4100
Alexandria, VA 22314
703.746.HELP

ተገንዝበው ይቆዩ!

@AlexandriaVATES

Para más información en Español
ለበለጠ መረጃ በአማርኛ
alexandriava.gov/LeafCollection

የአሌክሳንድርያ ከተማ

# ከፎል እስከ ኦተምን

2023 የቅጠል ማሰባሰብ አቅርቦቶች፣
የምግብ ቆሻሻ ለመቀነስ ጠቃሚ ምክሮች፣
እና በፎል/ጸደይ ወቅት ወደ ብስባሽነት መቀየር።

## አሌክሳንድርያ የምግብ ቆሻሻን እንቀንስ!

ምግብ ሲባክን፣ በተጨማሪም ሀብቱን ያባክናል ። ችግር መፍጠር ብቻ አይደለም፣ የንግድ ድርጅቶችን እና የነዋሪዎችን ገንዘብ የመቆጠብ እድልም አጥተናል፥ **ብክነትን በማሳነስ ወጪንም ያሳንሱ** – የሚጠቀሙትን የምግብ መጠን ብቻ በመግዛት፣ ትንሽ ወጪ ማውጣት እና ብክነትንም መቀነስ ይችላሉ።

### ስማርት ግብይት

የሚፈልጉትን ብቻ ይግዙ፣ እንዲሁም በመጀመሪያ ለማዕድ ቤትዎ የሚሆንዎትን ይግዙ። በዚህ ሳምንት ውስጥ በቤት ውስጥ ምን ያህል ጊዜ ምግብ እንደሚመገቡ እና ቀጥሎ አስቤዛ ለመግዛት ገበያ የሚሄዱት መቼ እንደሆነ ያስቡ።

### ስማርት ዝግጅት

በቀላሉ የሚበላሹ ምግቦችን ከገዟቸው በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ያስተካክሉ። ይህን ማድረግ በሳምንቱ መጨረሻ አካባቢ ምግቦችን ለማዘጋጀት ቀላል የሚያደርገው ሲሆን፣ ይህም ጊዜን፣ ጥረትን እና ገንዘብን ለመቆጠብ ያስችላል።

### ስማርት አቀማመጥ

የትኞቹ ፍራፍሬዎች እና አትክልቶች ፍሪጅ/ማቀዝቀዣ ውስጥ ወይም ውጭ ሆነው ለረጅም ጊዜ መቆየት እንደሚችሉ ይወቁ። በከፍተኛ ደረጃ ትኩስ ሆነው እንዲቆዩ በሚችሉበት ሁኔታ በማስቀመጥ የበለጠ ጣዕም እንዲኖራቸው እና ለረዥም ጊዜ እንዲቆዩ ያድርጉ።

### ስማርት ቁጠባዎች

የሚገዙትን ምግብ ይመገቡ። ስለተረፉ እና ለረጅም ጊዜ ስለቆዩ ምግቦችን ጥንቃቄ ያድርጉ። የምግብ ብልሽትን ለመከላከል፣ ቤተሰቦች ብዙም ሳይቆዩ መበላት ያለባቸውን ምግቦች ለማስቀመጫ የሚሆን በማቀዝቀዣው ውስጥ የተወሰነ ቦታ እንዲመድቡ እና ይህንን የሚያስታውሳቸው ምስላዊ ማስታወሻ እንዲለጥፉ ይበረታታሉ።

### ምግብ ይለግሱ

ከመጠን በላይ የሆነን ምግብ ለ**ሌሎች ሰዎች ይለግሱ!**
Food Hubs እድሜን፣ የዜግነት ሁኔታን፣ የኋላ ታሪክን እና የገቢ ሁኔታን ሳይመለከት ለአሌክሳንድሪያ ከተማ ነዋሪዎች ነጻ ምግብ ያቀርባል።

በቤት ውስጥ የምግብ ብክነትን ለመቀነስ የሚያግዙ ተጨማሪ ምክሮች እና ግብዓቶችን ለማግኘት alexandriava.gov/go/4260 የሚለውን ድረገጽ ይጎብኙ።

# 2023 የቅጠል ማሰባሰብ መመሪያ

## የቅጠል ማሰባሰብ


**ከጥቅምት መጨረሻ እስከ ጥር** ድረስ የከተማ አስተዳደሩ ቡድኖች የቅጠል ማጽጃ ተሽከርካሪዎችን በየስፍራው የሚያንቀሳቅሱ ሲሆን፣ የወረቀት ቅጠሎችን ቦርሳዎች ያሰባስባሉ።


### በንፋስ የሚሰራ የቅጠል ማጽጃ

አሌክሳንድሪያ በአራት የቅጠል ማሰባሰቢያ ዞኖች የተከፋፈ ለች ስትሆን፣ እያንዳንዳቸው የየእራሳቸው የማስጀመሪያ ቀን አላቸው። የከተማዋን ቆሻሻ የማሰባሰብ ሂደት ላይ የሚሳተፉ ነዋሪ ዎች በቅጠል ማሰባሰቢያ ወቅት ሶስት መለፊያ ጊዜዎች ያገኛሉ። ሠራተኞች በዞንዎ ውስጥ ከሁለተኛው እና ሶስተኛው ማለፊያ ዎች፣ የመጀመሪያዎቹን ቀኖች የሚዘረዝሩ ምልክቶችን ይለጠፋሉ። ነበር ግን መጥፎ የአየር ሁኔታ የጊዜ ሰሌዳ መዘግየትን ሊያስከ ትል ይችላል። ሰራተኞች በአንድ ዞን ውስጥ ማጽዳትን ለመጨረስ በርካታ ቀናት ሊወስድባቸው በመቻሉ የተነሳ፣ በእርስዎ አካባቢ መሰባሰብ በሚጀመርበት እለት ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ባይመ ለከቱ እንኳ ስጋት ሊገባዎት አይገባም።

### እንዴት እንደሚዘጋጁ፥

- ከሚያሰባስቡበት ቀን ቀድመው ቅጠሎችን ያራግፉ።
- በመንገድ ጠርዝ ላይ ቅጠሎችን አራግፈው በክምር አንድ ላይ ያድርጉ። ይህም ሰራተኞች በፍጥነት እና በውጤታማነት ለማሰ ባሰብ ያስችላቸዋል።
- ድንጋዮች፣ ስንጥሮች፣ ቅርንጫፎች፣ እና ሌሎች ቆሻሻዎችን ያስወግዱ። እነዚህ ነገሮች መሳሪያዎችን ሊያበላሹ እና በሰራተ ኞቻችን ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ናቸው።
- ቅጠሎችን በጎርፍ መውረጃ ወይም የውሃ ቆጣሪ ክዳን ፊት ለፊት አያስቀምጡ።
- የቆሙ ተሽከርካሪዎችን ከቅጠል ክምሮች ያርቁ።
- ቅጠሎችን በጥገና ጊዜ መግቢያዎች ወይም በጥገና መንገድ ላይ አያራግፉ። በጥገና ጊዜ መግቢያዎች ውስጥ ያሉ የተበታተ ኑም ሆኑ በቦርሳ ውስጥ ያሉ ቅጠሎችን አናሰባስብም።




*መንገድዎ አዋሳኝ ስፍራ የሚገኝ ከሆነ፣*
*የመንገዱን አማካይ እንደ አካፋይ ይመልከቱት።*

## የመጀመሪያ የማለፊያ ቀናት

| | |
|---|---|
| ጥቅምት 30 | ዞን 2 |
| ህዳር 3 | ዞን 3 |
| ህዳር 9 | ዞን 4 |
| ህዳር 13 | ዞን 1 |

| | |
|---|---|
| ዞን 5 | (ኦልድ ታውን) |
| ክፍል 5A | ጥቅምት 30 |
| ክፍል 5B | ህዳር 6 |
| ክፍል 5C | ህዳር 13 |
| ክፍል 5D | ህዳር 17 |

**የመኖሪያ አካባቢ የቅጠል ማሰባሰብ መረጃዎችን ለማግኘት እና የቤት አድራሻን መሰረት አድርጎ የማ ሰባሰብ ጊዜ ሰሌዳን ለመመልከት QR code ስካን ያድረጉ.**

## የቅጠል ማጠራቀሚያ ከረጢቶችን ማንሳት

ቅጠል የተሰባሰበባቸው ረጢቶች በመደበኛው የቆሻሻ ማንሻ እለት ከመንገድ ዳይ እንዲሰባሰቡ ይደረጋል። የቅጠል ከረጢቶችን መሰብሰብ **ጥቅምት 30 ጀምሮ እስከ ጥር መጀመሪያ** ድረስ ይቆያል።

ሊበሰብሱ የሚችሉ የወረቀት ከረጢቶችን በመጠቀም ከተማዋ ቅጠሎችን በማበስበስ እንደገና እንደ አፈር ማዳበሪያ ጥቅም ላይ እንድታውል ያስችላታል። ሊበላሹ የሚችሉ የፕላስቲክ ከረጢቶ ችን ጨምሮ በፕላስቲክ ከረጢቶች ውስጥ ያሉ ቅጠሎች በኮሻንታ ኢነርጂ ከቆሻሻ የማምረቻ ፋብሪካ ውስጥ እንደ ቆሻሻ ይጣላሉ።

### ለተጨማሪ መረጃ

ቀጣዩን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፥**alexandriava.gov/LeafCollection** ወይም የቅርብ ጊዜ መረጃ ለማግኘት በቀጣይ ቁጥር ይደውሉ፥ **Alex311 at 703.746.4311**

**በከተማዋ በነጻ የሚሰጡ ከረጢ ቶች ቅድሚያ የመጡት ቅድሚያ በሚስተናገዱበት አሰራር ይቀ ርባሉ። ወሰን፥ 15 ከረጢቶች ለአንድ ነዋሪ፣ በአንድ ጉብኝት።**
**ከረጢቶች ጥቅምት 16 ጀምሮ በሚከተሉት አድራሻች ማግኘት ይችላሉ፥**

**የከተማው አዳራሽ – ዋናው ሎቢ**
301 KING ST.
ከሰኞ-አርብ
7 a.m. – 8 p.m.

**Charles Houston Recreation Center**
901 WYTHE ST.
ከሰኞ-ቅዳሜ
9 a.m. – 9 p.m.
እሁድ፣ 1 p.m. – 5 p.m.

**የአሌክሳንድርያ ከተማ Self-Serve Shed**
ROTH ST. & BUSINESS CENTER DR.
24/7 አገልግሎቱ ይገኛል

**Mount Vernon Recreation Center**
2701 COMMONWEALTH AVE.
ከሰኞ-አርብ
9 a.m. – 9 p.m.
ቅዳሜ፣
9 a.m. – 6 p.m.

**Patrick Henry Recreation Center**
4653 TANEY AVE.
ከሰኞ-አርብ
9 a.m. – 9 p.m.
ቅዳሜ፣ 9 a.m. – 6 p.m.

**Chinquapin Recreation Center**
3210 KING ST.
ከሰኞ-ሀሙስ
6 a.m. – 9 p.m.
አርብ፣ 6 a.m. – 6 p.m.
ቅዳሜ እና እሁድ፣
8 a.m. – 6 p.m.